ታሕሳስ ፳፱ ቀን ፳፻ ዓ.ም (ጃንዋሪ 7/2008)

# ኢትዮጵያኖች በሞላ! እንኳን ለኢትዮጵያ ገና አደረሳችሁ

## እዞም ተጋዳላይ ተጋደልቲ እንታይ ጉዱ?

### ቂ ቂ ቂ ቂ ቂ ምስኪን !

ከአያልነሽ

## ክፍል 2

ጥያቄ፥ ወደ ወይዘሮ አረጋሽ እንሂድና አሁን እንግዲህ እንደተባለው በመንግስታዊ አወቃቀር ደረጃ ልዩነት ያላችሁ አይመስለኝም፤ አሁን ካለው መንግስት ጋር። ለምሳሌ "በኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት" ውስጥ የሰፈረው የብሔር ብሔር-ሰቦች ራሳቸውን ችለው ማስተዳደር እስከመገንጠል ድረስ የሚለው አለ፤ አሁንም ይሄ እስከመገንጠል ድረስ የሚለውን ብዙ ሰው በጥሩ ዓይን አይመለከተውም። ሊከፋፍል ይችላል፣ አደገኛ ነው የሚል አስተሳሰብ አለና እናንተ አሁን ይሄን ትደግፋላችሁ ማለት ነው ወይዘሮ አረጋሽ?

የቸዝ ጠጠር የሆነችው "የአረና ትግራይ" መሪ አርጋሽ አዳነ እንዲህ ብላለች። በፕሮግራማችን ላይ "በመርህ ደረጃ" ተቀብለነዋል በማለት አስታኛለች ። ውይ! አፈ ቁርጥ ይበል የት አባቱ ልግባ አረናዎች? በመርህ ደረጃ! ገብሩ ሆነ አረጋሽ የሚጠየቁትን ማንኛውንም ጥያቄ ለመመለስ ከመለስ ትእዛዝ ውጭ ሆነው መናገር አይችሉም። መብትም ሆነ ነፃነት የላቸውም። ተደራጅተናል ብለው ሲመጡም በመለስ ቀጭን ትእዛዝ ነው። ይህንን እነርሱም ያውቁታል፣ እኛም አናጣውም። የሆኖ ሆኖ ግን እነ ገበሩ አስራት ለተጠየቁት ጥያቄ በማር ቀብተው ለማጉረስ የሞከሩትን ዝባዝንኬያቸውን አሳጥሬ እነርሱ በስድ ንባብ ያቀረቡትን መልስ እኔ በዚህ መንገድ አስፍሬዋለሁ።

ዓዋአሎምም ቢሆን ብፃይ/ጓዳችን ነው፣
ዓለምሰገድ ቢሆን ቁርጥ ልጃችን ነው፣
ተወልደም፣ ቢተውም አብሮን የደማ ነው፣
መለስም "ለዓቦዬ" ጀሮውን ቢሰጠው፣
እኛ ቂም የለንም ቃልህ ቃላችን ነው።

በቀነ ጎደሎ ነፋስ ቢገባብን፣
ጊዜያዊ ኩርፊያ ነው፣
"አማራ" እኮ ብሏል ጠቡ የሥጋ ትል ነው፣
ይሄን እንዳትረሳ ቃልማ ማተብ ነው፣
ሞኝ-ቂል አይደለንም ሁሉንም የምንተው፣
ማተቡን ያሰርነው ደደቢት ዋሻ ነው፣
39-ኝን አንቀጽዋን አስምረን እዚያችው መቆም ነው።

ወይ መዓልቲ!

እነ ገብሩና ስዬ አብርሃ ወደ አውሮፓና አሜሪካም የሚመላለሱት በመለስ ትእዛዝ ነው። "አረና" የተባለውን ስም አሸክሞ በዚህ ስም የሚሰሩትን ሥራ ሰጥቷቸዋል። ድርጅታቸውን የመሰረቱትም እንዲሁ በትእዛዝ ነው። መለስ

ከግንቦቱ ምርጫ በኋላ በመላው ኢትዮጵያ ህዝብ እየተጠበሰና ፊትህን አንየው በተባለበት ሀገር፤ እነ ገብሩ አሥራት ንብረታቸው ሳይነካ፣ እስካሁን ቁጭ ብለው የሚከፈላቸውን ደሞዝ ያለጭንቅ ሲበሉ ኖረዋል። መለስ ዛሬ ሲፈልጋቸው ደግሞ የጭንቁ ጊዜ ነውና በመለስ ስቃይ ወቅት እነ ገብሩ አሥራት ተንጋሎ ለመብላት አይፈቀድላቸውም። የመለስ ዕቃዎች ናቸውና አግልግሎታቸውን ሲፈልግ መለስ በፈለገው ጊዜና ሰዓት ወደ ፈለገው ቦታ ያንቀሳቅሳቸዋል ቼዝ ጠጠሮቹን። የማዘዝ ሙሉ ሥልጣን አለው - ጠጠሮችን በፈለገው ቦታ ለማንቀሳቀስ ። ቁጭ ብለው ''ብጻይ መለስ'' እያሉ የሰጡት ሥልጣን አለውና የቸዝ ''ንጉሥ'' ነው። ስለዚህ እንዳይሞት ጠጠሮቹን ማንቀሳቀስ፣ ቸክ ሲባል ደግሞ ሰዎችን ቀይሮ ስማቸውንም አድሶ ሌሎችን ማንቀሳቀስ ሃ! ሃ! ሃ! ሃ! ሃ!

አዲሱን ድርጅታቸውን የመሰረቱትም ትግራይ ውስጥ ሳይሆን አዲስ አበባ ነው። ስለ ድርጅታቸውም የሚናገሩት ትግራይ ውስጥ ሆነው ሳይሆን፣ አዲስ አበባ ሆነው በተለያዩ ነፃ ራዲዮኖች እየቀረቡ በሚገልጹትና በሚልኩት ወረቀት ነው። የዛሬን አያድረገውና ከዛሬ 35 ዓመት በፊት ትግሉን ሲጀምሩ፣ ከትግራይ ምድር ተነስተው፣ የትግራይ ወጣቶችን በተሳሳተና በተዛባ ታሪክ መግበው፣ ከፊትና ከኋላ (ከጀርባ በሻዕቢያና በራሳቸው) ጥይት እየመቱ፣ ከፊት ለደርግ ጥይት እየማገዱ (ሓውዜንን ያስታውሷል) ነበር የ''አማራ ኩራኩሩ''ወደ እሚሏት የኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ የገቡት። ያኔ ትግል በጀመሩበት ወቅት ትግራይ ውስጥ ከእነርሱ ውጭ፣ ሌላ ኃይል እንዳይንቀሳቀስ ስም እየለጠፉና እያወጡለት ሲያጠቁ ኖረዋል። ሥልጣን ከያዙም በኋላ ቢሆን ትግራይ ውስጥ ከሕወሓት/ወያኔ ሌላ የተለየ ድርጅት ነበር? አሁንስ አለ? ብላችሁ ጠይቋቸው እነ ገብሩ አሥራትን። ዛሬም ''ከመንግሥታቸው በመንግሥታቸው'' ሲገፉ፣ ከለላና መጠጊያ የሆናቸው ትናንት እነ ገብሩ አሥራት፣ ስዬ አብርሃ የገፉት፣ አገሬ ኢትዮጵያ በማለቱ በእነርሱ የተፈረደበት ''ኩራኩር አማራ'' እያሉ አንገቱን ሊያስደፉት የሞከሩት፣ በመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ ነው የተጠለሉት። ዛሬም የሚገኙት በዚህ ሕዝብ ውስጥ መሃል ነው። መለስ ወደሚያዛቸው ቦታ ለመንቀሳቀስ የሚንደረደሩትም፣ ከትግራይ ወይም ከአሥመራ ሳይሆን ''ኩራኩር አማራ'' ከሚሉት ከአዲስ አበባ ነው። ለትግራይ ሕዝብ ነው የታገልነው፣ ለአንተ ብለን ነው መከራ ያየነው ሲሉት የነበረው የትግራይ ህዝብ፣ ትናንትናም በእነ ገብሩ አሥራትና ገብር አበሮቹ ቁጥጥር ሥር የወደቀ ነበር። ዛሬም ቢሆን በክፍፍሉ ወቅት ከእነርሱ ጋር ቆመው የነበሩት በኋላ ግን የካዷቸው እነ ቅዱሳን ነጋ (የስብሃት ነጋ እህት) እና ባለቤቷ ፀጋዬ በርሄ፣ በትግራይ ክ/ሃገር የአቶ ገብሩ አሥራትንና የአረጋሽን ቦታ ተረክበው ትግራይንና የትግራይን ሕዝብ በቁጥጥራቸው ሥር አድርገውት ይገኛሉ። ይሄ እውነት አይደለም? ብላችሁ ጠይቋቸው፤ ግን በድብቅ ሳይሆን በአደባባይ። ነፃነትን የማያውቅ ስለ ነፃነት ሊያስተምር፣ ሊሰብክ አይችልም። እባካችሁ፤ የትግራይ ልጆች! እነስዬና አረናዎች ዛሬ ለእናንተ አውሮፓና አሜሪካ ላላችሁት የትግራይ ልጆች እየዞሩ የሚናገሩትን፣ ለትግራይ ሕዝብ ትግራይ ውስጥ መናገር ይችሉና አይችሉ እንድሆን እስቲ ጠይቋቸው? እንደ ልብ ትግራይ ውስጥ መዘዋወር ይችሉ ይሆን? ትግራይ ውስጥ ይሄንን የነፃነት ማጣት የሰራው ማን ነው? ብላችሁ

ጠይቋቸው። የትግራይ ህዝብ ልጆቹን ገብሮ፣ እነ ገብሩ አሥራትን ባለ ሃብት አድርጓቸዋል፤ ይሄ ሃቅ ነው። ያኔ በክፉው ዘመን እናንተ ስትራቡ፣ ከእናንተ አፍ ነጥቀው በሞታችሁ ሬሳችሁን በቪዲዮ ቀርፀው ሸጠው ሥልጣን ላይም ወጥተው ነበር። በዚያ አሰቃቂ የረሃብ ወቅት የሆነውንና የሆናችሁትን ከአብራካችሁ የወጡትን እነ አቶ ገ/መድህንን ጠይቋቸው፤ ያጫውቷችኋል። ግን በድብቅ ሳይሆን በአደባባይ። አሁን በአደባባይ እየዞሩ የሚናገሩት የአደባባዩን የምናውቀውንና የምታውቁትን ነው። እስከዛሬ ግን ያልነገሩንና ያልነገሯችሁን ይንገሩን። እኛ እንዳንጠይቃቸው "ኩራኩር አማራዎች" ናችሁ ብለውናል። እኛ እንዳንጠይቃቸው ለ"አባይ ኢትዮጵያ ነው የተጋደላችሁት" ይሉናል/ብለውናል። የገደልናችሁም፣ ያሰርናችሁም፣ ያሳደድናችሁም፣ በዚሁ ጥፋታችሁ ነው ይሉናል ዛሬም። ሌላም አለ። <u>ኢትዮጵያዊው ሁሉ በእኛ ላይ የተነሳብን "ትግሬ" በመሆናችን ነው ብለው እነ ስዬ አብርሃና</u> እነ <u>ገብሩ አሥራት፣</u> ከቀሪው ኢትዮጵያዊ ጋር እንዳትገናኙና እንዳንገናኛችሁ ፣ አጥሩን ሰርተው ያቆሙት፣ በሣርና በድንጋይ ሳይሆን፣ በደም ጎርፍ አጥለቅልቀው፣ በቂምና በጥላቻ፣ ብረት መዝጊያ ሠርተው ነው። ጠይቋቸው የትግራይ ልጆች አባካችሁ። ዛሬም እኛ እንዳንጠይቃቸው እነ ገብሩ አሥራት አሁንም በዚሁ "አማራ ኩራኩርነታችን" እንዳሰሩን ናቸው በልባቸው። ገና አልፈቱንም። የኤርትራና የትግራይ ህዝብ የተጋደለውና በደም ጎርፍ አጥለቅልቀው አጥር አበጅተው ያቆሙለት፣ አማራና ትግሬ ሆኖ ይሆን? ብላችሁ ጠይቋቸው በደንብ። ግን በምስጢር ሳይሆን በአደባባይ። ስለዚህ አጥሩንም የሠሩት እነርሱ ናቸው፤ አጥሩንም ማፍረስ ያለባቸው እነሱ (እነገብሩና ስዬ) ናቸው። አቦ! እኛማ እውነት መስሎን 3 አራት ጊዜ ሞተን አሳየን እኮ በሏቸው፤ የትግራይ ልጆች!!! በትግርኛ ተናጋሪውና በቀሪው ኢትዮጵያዊ መካከል የፈጠሩትን፣ የሰሩትን የቂምና የመፈራራት፣ የመጠራጠር ሰይጣናዊ ተግባራቸውን፣ ራሳቸው እንደገና በንጹሕ ልብ ታድሰው ያድሱት። ይሄን ሲያደርጉ ብቻ ነው እምነት የሚጣልባቸው፣ የምንጥልባችሁ በሏቸው። ይሄን ደግሞ ማድረግ ያለባቸው ከልባቸው ለራሳቸው ሳይሆን ለልጆቻቸው፣ ለልጅ ልጆቻቸው፤ ለራሳቸው ሳይሆን እንወድሃለን ለሚሉት ለዚያ ቅን ለሆነው ለትግራይ ሕዝብ ክብር ሲሉ ነው። አሁንም የምለው በቅንነት ሊያደርጉት ቀርጠው ይነሱ ነው። ከመለስ ጋር የተቀራርጥነው መለስ "ለትግራይ ሕዝብ ስላልቆመ ነው" ብለዋልና እነርሱ ለትግራይ ሕዝብ መቆማቸውን እነሆ ዛሬ በቂምና በበቀል ያጠሩትን ግንብ አፍራርሰው፣ ያበጣበጡትን፣ ያቀራረጡትን፣ እርስ በርስ እንዲፈራራና እንዳይተማመን፣ እርስ በርስ አብሮ አንዳይኖር ያደረጉበትን መረብ፣ በጣጥሰው ጥለው ሊያገናኙን ይጠበቅባቸዋል - እውነት ይሄን የሚፈልጉ ከሆነ። እውነት ከልባቸው ከሆነ፣ ወንድማማችና፣ ሥጋ ዘመድ የሆኑ፣ የቅርብ ጎረቤታሞችና አብረው የኖሩና የተዋለደው የኤርትራና የትግራይ ሕዝብ የሚኖረውና የሚገኘው እዚያው እነርሱ ከአሉበት፣ እነርሱ ጥግ ነው - ሕዝብን ከሕዝብ ለማስታረቅ ከሆነ አላማቸው። እዚህ ውጭ ላለነው የእነርሱ መምጣት አያስፈልግም ባይ ነኝ ሌላ ሥራ ከሌለ በቀር።

አሁን በያዝነው የፈረንጆች አዲስ ዓመት መግቢያ ጃንዋሪ 5 ላይ በአሜሪካ በ"ኢትዮጵያን ሪቪው" ራድዮ አማካኝነት በቀጥታ የተላለፈውን የአቶ ሥዬ አብርሃን ንግግር በሙሉ አዳምጨዋለሁ። ስዬ ረዥም ንግግሩን ያደረገው

በኢትዮ/ኤርትራ ጉዳይ ላይ ሲሆን የኤርትራን መገንጠል (እንደ አገር መቆም) ተገቢ ነው ብሎ፤ ይሁን እንጅ ይላል ከዚያ ተከትሎ የመጣው ጣጣ ግን ትክክል እንዳልሆነ አስምሮበታል። ይህ ትክክል አይደለም የሚለው ጉዳይ በአብዛኛው (ባድሜንም) ጨምሮ ከዚያ ጋር የተያያዘውን ጉዳይ ሲሆን፣ ባድሜ 100 ሽህ ሰው በልታ ራሷን ሳታድን፣ ለእነርሱም ከሥልጣናቸው መባረር ምክንያት ሆናለችና እጅግ ሰፊ ጊዜውን ሰጥቶ ሊያብራራ ሞክሯል።

የስዬ ንግግር ከላይ እንዳልኩት በሰፊት ያተኮረው በኢትዮ/ኤርትራ ጉዳይ ላይ ይሁን እንጅ ከጦርነቱ በኋላ በተከተለው መዘዝና በመጨረሻም ስለራሱ ታሪክ በመጠኑ የሚዳስስ ነበር። ስዬ ከህወሓት/ወያኔ ጋር ባሳለፈው ዘመኑ የነበረውን ሚና አንስቶ፣ በመጨረሻም የታገለበትና/የታገለለት ድርጅት ሕወሓት/ወያኔ፣ እስር ቤት የወረወረው ከነመላ ቤተሰቡ መሆኑን በቁጭት ገልጧል። ለእስር የተዳረገውም በሙስና ሳይሆን ከእነ መለስ ጋር ባለው የፖለቲካ ልዩነት ምክንያት ሳቢያ በቂም መሆኑንም፣ አስርግጦ አልፏል። የእኔ በእነ መለስ መታሰር ይላል አቶ ስዬ፣ የእኔ በእነ መለስ መታሰር "ለኢሕአዴግ" አመራሮችና አባሎች መቀጣጫ እርምጃ ነው፤ አደብ ግዙ፣ እንኳንስ ለእናንተ ለስዬም አልቀረለትም የሚል መልእክት ለማስተላለፍ ታስቦ የተደረገ ነው በማለት፣ ድርጊቱን አጥብቆ ኮንኖታል። የሚገርም ነው። አቶ ስዬ እሥሩ እጅግ እንዳመመውና ሊያሳስረው የማይበቃ፣ ፍትኃዊ ያልሆነና አግባብ የሌለው መሆኑንም አስምሮበታል። ይቅርታ ይደረግልኝና አንድ ጥያቄ ይፈቀድልኝ። ስዬ፣ እሥሩ አንተ ጋ ሲደርስ ይሆን ያመመህ ብዬ ብጠይቀው ነውር አለበት? አልመሰለኝም። መጠየቅ የማይከለከልበት አገር ውስጥ ነውና የምኖረው፣ መጠየቁ ሥጋት የለውም። እኔ ማንም ሰው ያለ አግባብ መታሰሩንና አለአግባብ መንገላታቱን አጥብቄ የምቃወምና ድርጊቱንም አጥብቄ የምኮንን ነኝ። በዚህ ኢ-ሰብዓዊ በሆነና ፍትሃዊ ባልሆነ መንገድ ለተሰቃዩና ለተንገላቱ ማናቸውም ሰዎች ሃዘኔ ከባድ ነው። አቶ ስዬ ግን በቀረጸው ሕግ ቢያንስ "ፍትህ" ደጅ ቀርቦ/ደርሶ በነጻ ተለቋል። እነ አቶ ስዬና መሰሎቹ በቀረጹት ሕገ-ወያኔ ደግሞ ፍትህ ደጅ ሳይደርሱ የስንቱ ሰው ሕይወት ተቀጥፏል? እነ አቶ እስዬ ሥልጣን ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ  በኢትዮጵያ ውስጥ ያልተደረገና ያልተፈጸመ ግፍ የለም። ለምሳሌ አቶ ተስፋዬ ታደሰ በጠራራ ጸሐይ በወያኔ ታጣቂዎች በጥይት ተደብደበው ሬሳቸው መንገድ ላይ ተሰጥቷል። አቶ ተስፋዬ ታደሰ የልጆች አባት ነበሩ።  በጥይት ተደብድበው ሕይወታቸው እንዲያልፍ ያስደረገው ጥፋታቸው "ሙስና" ሳይሆን ኢትዮጵያዊነት ሆኖ መገኘት ነበር። ጓዳችን ጋይም ገ/እግዛብሐር በጥይት ተደብድቦ ሬሳው የተሰጣው አዲስ አበባ በአደባባይ ነበር። ጥፋቱ የትግራይ ልጅ ሆኖ ኢሕአፓ ሆኖ መታገሉ ነበር፤ እነኝህ ሁሉ ፍትህ ደጅ ሳይቀርቡ በጥይት ፍርዳቸውን ያገኙ ናቸው። በነገራችን ላይ ጋይም 2 ጊዜ ከወያኔ እስር ቤት ያመለጠ ጀግና ነበር። አቶ አሰፋ ማሩም እንዲሁ በወያኔ ታጣቂዎች ነበር ቤታቸው በር ላይ በግንባራቸው ተመትተው በአፋቸው የተደፉት። አቶ አሰፋ ማሩም የልጆች አባት ነበሩ። ፕሮፌሰረ አሥራት ወልደየስ በወያኔና በሻዕቢያ በተቀነባበረ ወጥመድ 5 ዓመት ታሰረው በእስር ቤት ሲማቅቁ፣ በከባድ ሕመም ላይ ወደቁ። የሚሞቱ መሆናቸውን ሲረጋገጠ ደግሞ የእስር ጊዜያቸውን ሳይጨርሶ ለሕኪምና ወደ ውጭ ሄደው እንዲሞቱ ተደርጓል። ፕሮፌሰር አሥራት

በሰኔው "የሽግግር መንግሥት ጉባዔ" ላይ የአዲስ አበባ ዩኑቨርስቲ መምህራኖችን ወክለው በመገኘት፣ ከዚያ ሁሉ ጉባዔተኛ መሃል፣ በኢትዮጵያ ሕልውናና ሉዓላዊነት ላይ የተሸረበውን ሴራ አውግዘው ይህ ጉባዔ ይህን መሰል አደገኛ ጉዳይ ለመወሰን ሥልጣን የለውም በማለታቸው ነበር በእነሰዬ ድርጅትና በሻዕቢያ እጅ ላይ የወደቁት። ፕሮፌሰር አሥራት ይህንን የ "ሰኔ ገባዔ" ረግጠው ሲወጡ ምክነያታቸው በኢትዮጵያ ሕልውና ላይ ያነጣጠረ አደገኛ ሂደትን ተቀምጬ አልወስንም በማለታቸው ነበር ። አቶ ስዬና ባልደረቦቻቸው ያኔ በኢትዮጵያ ስም "የኢትዮጵያ መንግሥት" ባለሥልጣን ነን ባሉበት ወቅት ያሻቸውን ሲወስኑ፣ ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ ለሕይወታቸው መጥፊያ የሆነውን ይሄንን ጉዳይ ተቃውመው ሲወጡ፣ በእነሰዬ የተለጣፈላቸው ታፔላ "አማራ" የሚል እንደነበረ አይዘነጋም። ይህ የተቀነባበረ ሴራ ከሻዕቢያው መሪ ኢሳያስ አፈወርቂ "ልዩ ኃይል" ጋር በመተባበር ነበር ፕሮፌሰር አሥራትን አገራቸው ውስጥ ያሳደዷቸው። እንደዛሬው ሳይሆን ያኔ ኢሳያስ አፈወርቂ የኢትዮጵያም የኤርትራም "መንግስት" ነበርና እስኪጣሉ ድረስ። የፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስን ሕይወት የቀጠፈውና ለሕይወታቸው መጥፊያ የሆነው ይህ የሰኔው "የሽግግር መንግስት ጉባዔ" በእነ ገብሩ አስራትና በእነሰዬ አብርሃው ሕወሓት/ወያኔ ድርጅት ሲዘጋጅ በዚህ ጉባዔ ላይ፣ ቀይ ምንጣፍ ተነጥፎለት፣ ሞቅ ባለ ግብዣና ከልዩ ጥበቃ ጋር በሙሉ ልብ ያለምንም ጭንቀት እንዲሳተፍ "የክብር" እንግዳቸውና ተሳተፊ ሆኖ የተገኘው ኢሳያስ አፈወርቂ ነበረ። ልብ በሉ፣ ዛሬ ዐይንህን ላፈር የሚሉት የያኔው "የመንግስታቸው የክብር እንግዳ" የነበረው ኢሳያስ አፈወርቂ። ወይ ጊዜ!።

በርካታ ኢትዮጵያኖች የተገደሉበትና ደብዛቸው እንዲጠፋ የተደረገበት፣ አርበኛው ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስንም ጨምሮ በሻዕቢያና በወያኔ ሴራ እየተሳደዱ ለሞት ሲዳረጉ፣ ጥፋታቸው ሆኖ የተገኘው ኢትዮጵያዊ ሆነው በመፈጠራቸው ነበር። ታዲያ ይሄን ጊዜ ምን ትሉታላችሁ ወገኖቼ ?እኔ የምለው ዘመነ-ጉግማንጉግ አጀብ! እነ ስዬ አብርሃ በ1984 ዓ.ም የካቲት ወር(ኢትዮ.አ) ወይዘሮ ለተብርሃን መንግስተዓብን ከወረዳ 11 ቀበሌ 16 በወያኔ ታጣቂዎች አዲስ አበባ ተጠልፈው በአስቃቂ ግብረ ሰይል (ቶርቸር) ተስቃይተው፣ እስከዛሬ ደበዛቸው የጠፋውና ያልተገኘው "አማራ" ስለሆኑ አልነበረም። አቶ ሐጎስ አጽብሃ (ቀድሞ የህወሓት/ወያኔ አባል የነበሩ) ኗሪነታቸው ሱዳን ውስጥ የነበረ በ1981 ዓ.ም (ኢትዮ.አ) ከሱዳን ተጠልፈው እስከ አሁን በትግራይ ጉድጓድ እስር ቤት ውስት የሚማቅቁት "አማራ" በመሆናቸው አይደለም። ብዙ መጥቀስና መዘርዝር ይቻላል። አቶ ስዬ "ስለ ራሴ ትንሽ ላውራ" ብሎ ስለራሱ ታሪክ በሚያወራበት ጊዜ ከእርሱ ጋር ታስሮ እስካሁን ድረስ ሳይፈታ ስለቀረው ወንድሙም ምርር ብሎ አፅንዖት ሰጥቶ ገልጧል። ምን አለ? .......ተከታዩን በሚቀጥለ